የሰ/መ/ቁ. 29369

መጋቢት 9 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሆለታ ግብርና ምርምር ማዕከል ነ/ፈጅ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተመስገን አድነው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ተከሳሽ በከሳሽ መ/ቤት ተቀጥረው ሲሠሩ ከሳሽ መ/ቤት የሚሠራውን የምርምር ሥራ በአዳዲስ ሳይንሳዊ ዕውቀት ለማሻሻል እንዲቻል ተከሳሽ በሀረማያ ዩኒቨርስቲ በኤም-ኤሲ-ሲ ደረጃ እንዲማሩ የተደረገ ሲሆን በትምህርት ላይ በነበሩበት ጊዜም የ24 ወር ደመወዝ ብር 23,520 (ሃያ ሦስት ሺ አምስት መቶ ሃያ ) ተከፍሏቸዋል፡፡ ከዚህም ሌላ ተከሳሽ ባቀረቡት ፕሮፖዛል መሠረት ብር 54,409 (ሃምሳ አራት ሺህ አራት መቶ ዘጠኝ ብር ) ከሳሽ ለዩኒቨርስቲው ከፍሎላቸዋል፡፡

ተከሳሽ ወደ ትምህርት ከመሄዳቸው በፊት ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ወደ ከሳሽ መ/ቤት ተመልሰው በትምህርት ላይ ለቆዩባቸው ለእያንዳንዱ ወር የ3 ወራት የሥራ አገልግሎት ለመስጠት ጥቅምት 13 ቀን 1993 ዓ.ም የውል ግዴታ ገብተው የነበረ ሲሆን ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኃላ ግን የጀመሩትን የምርምር ሥራ ትተው ሥራቸውን በፈቃዳቸው ለቀው የሄዱ ስለሆነ እንደውሉ ተገደው እንዲፈጽሙ ተከሳሽ በውሉ መሠረት ለመፈጸም ፈቃደኛ ካልሆኑ ከሳሽ መ/ቤት ለትምህርቱ የከፈለላቸውን በድምሩ



ብር 77,929.00 (ሰባ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ዘጠኝ ብር) እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃም ለተከሳሽ ደርሶ በሰጡት መልስ ከሳሽ ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ የውልም ሆነ የሕግ ድጋፍ እንደሌለው በመዘርዘር ክሱ ከኪሣራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ከሳሽ ባቀረበው ክስ ተከሳሹ እንደ ውሉ ተገዶ ይፈጸምልኝ በማለት የጠየቀውን በተመለከተ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1776 (1) አኳያ ተቀባይነት የለውም ካለ በኂላ ከሳሽ በአማራጭ የጠየቀውና ለትምህርት ተብሎ የተከፈለው ውጭ ሊተካልኝ ይገባል የሚለውም የኪሳራ ክፍያ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1771(2) ድንጋጌ መሠረት ውሉ በግዴታ እንዲፈፀም ወይንም እንዲፈርስ ከመጠየቅ ጋር ተያይዞ መቅረብ የሚገባው ሲሆን ከሳሽ ግን ውሉ እንዲፈርስ ባልጠየቀበት ሁኔታ ኪሳራ ሊከፍለው ስለማይችል ክሱ በአግባቡ አልቀረበም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348(1) መሠረት አጽንቷል፡፡

ይህ ችሎትም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካች ለተጠሪ አወጣሁት የሚለው ወጭ እንዲተካለት ያቀረበው አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ አግባብነቱ ለሰበር ቀርቦ ሊጣራ የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የሰበር አቤቱታውም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ የመሠረተው ከላይ እንደተጠቀሰው ተጠሪ በውሉ በገባው ግዴታ መሠረት በከሳሽ መ/ቤት እንዲያገለግል ይህ ተቀባይነት ካላገኘ የከሳሽን መ/ቤት ያገለግላል በሚል እምነት ለትምህርት የገንዘብ ወጭ የተደረገለት ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ ሊተካልኝ ይገባል በማለት ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1776 ላይ እንደተመለከተው የባለዕዳው ቀጥተኛ የውል ፈጻሚነት (Specific Performance) ጥያቄ ሊመጣ የሚችለው የውሉ አፈፃፀም ለባለገንዘቡ የተለየ ጥቅም የሚሰጠው ከሆነና የባለዕዳውንም የግል ነፃነት

የማይነካ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ እንደሆነ በግልጽ የተመለከተ ስለሆነና ዳኝነት የተጠየቀበትም ጉዳይ የባለዕዳውን /የተጠሪን/ የግል ነፃነት የሚነካ በመሆኑ ተጠሪ ውሉን ተገዶ እንዲፈጽም ይወሰንልን በማለት አመልካች ዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ የሚነቀፍ አይሆንም፡፡

በሌላ በኩልም በአማራጭ የጠየቀው ዳኝነት ተጠሪ በአመልካች መ/ቤት ማገልገል የለበትም ከተባለ ለትምህርት የወጣው ወጭ ሊተካልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

የሥር ፍ/ቤት ይህንን የዳኝነት ጥያቄ ሳይቀበለው የቀረው የኪሳራ ክፍያ ጥያቄ የሚቀርበው ለብቻው ሣይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1771 መሠረት አንድም ከውል ይፈጸምልኝ ጋር አሊያም ከውል ይፍረስልኝ ጋር እንጂ ብቻውን ስላልሆነ አመልካች ውሉ እንዲፈርስ ባልጠየቀበት ሁኔታ የኪሳራ ክፍያው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡

በእርግጥ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1771 (1) እና (2) መሠረት የኪሳራ ክፍያ ጥያቄ ከውል ይፈጸምልኝ ወይንም ይሰረዝልኝ ጋር ተጣምሮ ሊቀርብ እንደሚችል መገንዘብ ቢቻልም በተያዘው ጉዳይ ከውሉ ባህሪይ አኳያ ተጠሪን አስገድዶ ማስፈጸም አይቻልም ከተባለ ውጤቱ የውሉን ቀሪ መሆን የሚያስከትል ስለሆነ አመልካች ደረሰብኝ የሚለው ኪሳራ ካለ ከመጠየቅ በስተቀር ውሉ እንዲሰረዝ መጠየቅ የሚጠበቅበት አይሆንም፡፡

በዚሁ መሠረትም አመልካች ሊተካልኝ ይገባል የሚለው ኪሳራ በአንድ በኩል ተጠሪ በትምህርት ላይ እያለ የተከፈለውን ደመወዝና በሌላ በኩልም ለዩኒቨርስቲው ተከፍሏል ያለውን ገንዘብ ነው፡፡

ተጠሪም በሰጠው መልስ በትምህርት ላይ እያለ ደመወዝ እንደተከፈለውና ሲማርበትም ለነበረው ዩኒቨርስቲ የትምህርት ወጪ መክፈሉን ሳይክድ ገንዘቡን ለአመልካች ለመመለስ ግዴታ የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

ሆኖም በግራ ቀኙ መካከል ጥቅምት 13 ቀን 1993 ዓ.ም የተፈረመውን ውል ይህ ችሎት አስቀርቦ እንደተመለከተው ተጠሪ በሥልጠና ለሚቆይበት የ24 ወራት ጊዜ አመልካች ደመወዝ እንደሚከፍለውና ለሥልጠና የሚያስፈልገውንም ወጭ አመልካች እንደሚሸፍን እንደዚሁም ከሥልጠናው በኋላ ለእያንዳንዱ ወር የሥልጠና ጊዜ ሶስት ወር ተጠሪ አመልካችን ማገልገል እንደሚጠበቅበት መስማማታቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡



በግራ ቀኙ በኩል የተደረገው ስምምነት ይህንን የሚመስል ከሆነ ተጠሪ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ አመልካችን ለማገልገል ፈቃደኛ ካልሆነ ኪሳራ የመክፈል ኃላፊነት እንደሚኖርበት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ነገር ግን የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ኪሳራ ለመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ክሱን ሳይቀበሉ መቅረታቸው ከውሉና ከሕጉ ጋር ያልተገናዘበ በመሆኑ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 06098 በጥቅምት 9 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 34431 በታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች ኪሳራ የመክፈል የውልና የሕግ ኃላፊነት አለበት ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ተጠሪ ለአመልካች መክፈል በሚገባው የካሣ መጠን ላይ ግን የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያልታየ ስለሆነ በዚሁ መሠረት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት መጠኑን በተመለከተ ከቀረበው ክርክርና ማስረጃ አኳያ ተመልክቶ እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተገዝቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዘ/ዘ